የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፪ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 36
ADDIS ABABA, 10th April, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፫/፪ሺ፲፯

የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ………….............................ገጽ ፲፰ሺ፪፻፲፩

## Content

Proclamation No. 1373/2025

System for the Intervention of the Federal Government in the Regions (Amendment) Proclamation ………………………Page 18211

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፫/፪ሺ፲፯

## የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ)

የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣው አዋጅ አተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እና በቀጣይ የአዋጁን አፈፃፀም ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

**፩.** **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፫/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.** **ማሻሻያ**

የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፱/፩ሺ፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

## PROCLAMATION No 1373/2025

## PROCLAMATION TO AMEND SYSTEM FOR THE INTERVENTION OF THE FEDERAL GOVERNMENT IN THE REGIONS

**WHEREAS,** it has been found necessary to amend the Proclamation to regulate the system of intervention by the Federal Government in the regions, in order to address the gaps observed in its implementation and make its subsequent implementation more effective;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be sited as the "System for the Intervention of the Federal Government in the Regions (Amendment) Proclamation No. 1373/2025."

**2. Amendment**

System for the Intervention of the Federal Government in the Region Proclamation No. 359/2003 is amended as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፫) ፣(፬) (፭) ፣ (፮) እና (፯) ተጨምረዋል፡-

“፫/ ጊዜያዊ አስተዳደሩ በክልሉ የሚቆየው ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ነው።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የፌደራል መንግሥቱን ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ካደረገው ሁኔታ ውስብስብነት አኳያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የጊዜያዊ አስተዳደሩን ቆይታ እስከ አንድ ዓመት ድረስ እንዲራዘም ሊወስን ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የጊዜያዊ አስተዳደር ቆይታ እንዲራዘም የተላለፈ ውሳኔ ለሁለተኛ ጊዜ ማራዘም ቢያስፈልግ አፈ-ጉባዔው ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘም ሊወስን ይቻላል።

፮/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) መሠረት የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች፣ ውሳኔው ከተላለፈ በኋላ በሚደረገው የፌደሬሽን ምክር ቤቱ መደበኛ ጉባዔ ቀርበው መፅደቅ ይኖርባቸዋል። የአፈ-ጉባዔው ውሳኔ በምክር ቤቱ ቀጣይ መደበኛ ጉባዔ ተቀባይነት ካላገኘ፣ ውሳኔው ውድቅ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር አራት ወራት ጊዜ ውስጥ ምርጫ ተደርጎ መደበኛ የክልል መንግሥት አስተዳደር መመሥረት ይኖርበታል።

1/ Sub-article (3) of Article 15 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-articles (3),(4),(5),(6) and (7) :

“3/ The Provisional Administration shall stay in the region for a period not exceeding two years.

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, the Speaker of the House of Federation may decide to extend the duration of the Provisional Administration for a period of up to one year in view of the complexity of the situation that has made it necessary for the federal government to intervene in the region.

5/ If an extension of the provisional administration’s term, as decided by the Speaker of the House of the Federation under Sub-Article (4) of this Article, requires a second extension, the Speaker may decide to extend it for a period not exceeding one year.

6/ Decisions made by the Speaker of the House of the Federation under Sub-Articles (4) and (5) of this Article shall be presented for approval at the next regular session of the House of Federation. If the Speaker’s decision is not approved by the House in its subsequent regular session, the decision shall be annulled, and a regular regional government shall be established through elections within four months from the date of annulment.

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬) ወይም (፭) መሠረት በፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ በሚተላለፍ ውሳኔ ወይም በንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የአፈ-ጉባዔውን ውሳኔ በማጽደቅ በሚሰጥ የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ውሳኔ ውስጥ ለፌደራል መንግሥት ጣልቃ መግባት ምክንያት የሆነውን ሁኔታ በዘላቂነት ለመቅረፍ እና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማጽናት አስፈላጊ የሆኑ፣ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሊመላከቱ ይችላሉ።”

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ከመጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**



7/ A decision by the Speaker of the House of Federation made under Sub-Articles (3), (4), or (5), or a decision by the House of Federation confirming the Speaker’s decision under Sub-Article (6) of this Article, may include provisions directing the provisional administration to undertake necessary measures to permanently resolve the circumstances that led to federal intervention and to strengthen the constitutional order."

3. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall be effective from April 1st day of 2025 on which it was apprroved by the House of People’s Representatives.

**Done at Addis Ababa, On this 10th Day of April, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**